የCharles ወንዝ ግብረ ኃይል ለዕኩል የወንዝ ተደራሽነት

የምክረ ሀሳቦች ሪፖርት

ማውጫ

1. ዋና ማጠቃለያ
2. መግቢያ
3. የCharles ወንዝ ግብረ ሀይልተግባራት
4. የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ
5. የግብረ ኃይሉ ገለጻዎች
6. የመጨረሻ የCRTF ምክረ ሀሳቦች
7. **የጋራ ሰብሳቢዎቹ የመዝጊያ አስተያየቶች**

ተጨማሪ ዝርዝሮች

ሀ. ክፍል 205
ለ. የCharles ወንዝ ግብረ ኃይል አባላት
ሐ. ሁሉም የተሳትፎ ሰነዶች
    ሀ. የትኩረት ቡድኖችና የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎች አጀንዳ
        i. የ2025 የመኸር ወቅት የትኩረት ቡድን አጀንዳ
        ii. የ2025 የመኸር ወቅት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ አጀንዳ
        iii. የ2026 የጸደይ ወቅት የትኩረት ቡድን አጀንዳ
        iv. የ2026 የጸደይ ወቅት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ አጀን
    ለ. በራሪ ጽሁፎች
        v. የ2025 የመኸር ወቅት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ በራሪ ጽሁፍ
        vi. የ2026 የጸደይ ወቅት የትኩረት ቡድን በራሪ ጽሁፍ
        vii. የ2026 የፀደይ ወቅት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ በራሪ ጽሁፍ
    ሐ. የዳሰሳ ጥናት መጠይቆች
        viii. የ2025 የመኸር ወቅት የዳሰሳ ጥናት መጠይቅ
        ix. የ2026 የፀደይ ወቅት የዳሰሳ ጥናት መጠይቅ
መ. የተሳትፎ ውጤቶች
    ሀ. ለ2025 የመኸር ወቅት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ የተሰጡ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች
    ለ. ለ2026 የፀደይ ወቅት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎች የተሰጡ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች
    ሐ. ከመኸር ወቅትና የፀደይ ወቅት የተሳትፎ ተግባራት የተገኙ ዋና ዋና ጭብጦች
ሠ. የDCR የተሳትፎና ስምሪት ወቅታዊ አሰራሮች
ረ. የ2025 የመኸር ወቅት የሳይት ጉብኝት ማስታወቻች

1. ዋና ማጠቃለያ

የግብረ ኃይሉ የጋራ ሰብሳቢዎች ምስጋና

የCharles ወንዝ ግብረ ኃይል ለእኩል የወንዝ ተደራሽነት (CRTF) የተቋቋመው የአካባቢ ጥበቃና መዝናኛ መምሪያ (DCR) በCambridge ውስጥ በLongfellow Bridge እና Eliot Bridge መካከል የCharles ወንዝ አካባቢ የቅርብ ነዋሪዎች፣ ተጠቃሚዎች ከሆኑና አካባቢውን በተመለከቱ ውሳኔዎች ተጽእኖ ከሚፈጠርባቸው ማህበረሰቦች ጋር የሚያደርገውን ተሳትፎ ለማጠናከር ነው። በዚህ ሥራ አማካኝነት ግብረ ኃይሉ በDCR ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ከማድረግ የሚገድቡ እንቅፋቶችን ለመለየት እና በታሪክ ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ ለተወከሉና ለተገለሉ ማህበረሰቦች ግንኙነትን፣ ስምሪትን እና የህዝብ ተሳትፎን የሚያሻሽሉ ምክረ ሀሳቦችን ለማዘጋጀት ይሞክራል።

በዚህ ጥረት ሂደት ውስጥ የግብረ ኃይሉ አባላት፣ ነዋሪዎች፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የኤጀንሲ ተወካዮች እና የአካባቢ አጋሮች በዚህ ሪፖርት ውስጥ ለተካተቱት ግኝቶችና ምክረ ሀሳቦች መረጃ ለመስጠት ከፍተኛ ጊዜያቸውን፣ ሙያቸውን እና ሀያው ተሞክሯቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። በስብሰባዎች፣ የትኩረት ቡድኖች፣ የዳሰሳ ጥናቶች፣ የህዝብ ሀሳብ መስጫ ስብሰባዎች፣ ቃለ መጠይቆች እና የስምሪት ተግባሮች ላይ የተሳተፉ ሁሉንም አካላት እናመሰግናለን። የእነሱ አስተዋጽኦዎች በCharles ወንዝ ኮሪደር ላይ የሚደረገውን ተሳትፎ ለማሻሻል እና በመላው ኮመንዌልዝ ውስጥ በDCR የህዝብ ተሳትፎ አሰራሮች ላይ ለሚደረጉ ሰፊ ማሻሻያዎች መረጃ ለመስጠት የተዘጋጁትን የተለያዩ ምክረ ሀሳቦች ቅርጽ እንድናስይዝ ረድተውናል።

ሥለ የCharles ወንዝ ግብረ ኃይል

የማሳቹሴትስ ሕግ አውጪ ለFY2025 በፀደቀው በጀት ክፍል 205 ስር የCharles ወንዝ ግብረ ኃይል ለዕኩል የወንዝ ተደራሽነትን አቋቁሟል። ግብረ ኃይሉ በCambridge የወንዙ ጎን በኩል በLongfellow Bridge እና Eliot Bridge መካከል ያለው የCharles ወንዝ አካባቢን ዕኩል ተደራሽነት በተመለከተ ጥናት እንዲያደርግ እና ለDCR ምክረ ሀሳቦችን እንዲያዘጋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

ሕጉ የግብረ ኃይሉ ምክረ ሀሳቦች DCR እንዴት በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ የአካባቢ ፍትህ መርሆዎችን በተሻለ ሁኔታ ማካተት እንደሚችል፣ እንዴት ለመንደሮቹ እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጥ ማስታወቂያና ግንኙነት ማሻሻል እንደሚችል፣ እና ውሳኔዎችን ለማሳለፍ በሚታሰብበት ወቅት እንዴት ትርጉም ያለው የህዝብ ተሳትፎን ማረጋገጥ እንደሚችል ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ማካተት እንዳለባቸው ያዛል።

ግብረ ኃይሉ በጋራ የተመራው በMetropolitan Area Planning Council (MAPC) በቀረበ ማመቻቸት እና የቴክኒክ ድጋፍ በኢነርጂና የአካባቢ ጉዳዮች (EEA) ሥራ አስፈጻሚ ጽህፈት ቤት፣ የአካባቢ ፍትህና እኩልነት ጽህፈት ቤት (OEJE) እና በDCR ነበር። አባላቱ የግዛት ኤጀንሲዎች፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የአድቮኬሲ ቡድኖች ተወካዮችን፣ እና ነዋሪዎችን አካቷል።

የተሳትፎ እና ስምሪት ተግባሮች

ግብረ ኃይሉ ለምክረ ሀሳቦቹ መረጃ ለማግኘት ከኦገስት 2025 እስከ ጁን 2026 ሰፊ የህዝብ ተሳትፎ ሂደት አካሂዷል። የተሳትፎ ተግባሮች የሚከተሉትን አካተዋል:

- አስራ አንድ የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎች፣

- አራት የትኩረት ቡድኖች፣
- አራት የህዝብ ሀሳብ መስጫያ ስብሰባዎች፣
- ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር የተካሄዱ የአንድ ለአንድ ውይይቶች፣
- የቤት ለቤትና የመንደር ውስጥ ስምሪት ጥረቶች፣ እና
- ሁለት የህዝብ ዳሰሳ ጥናቶች

በጋራ እነዚህ ጥረቶች በመቶዎች የሚቆጠሩ የማህበረሰብ አባላትና ባለድርሻ አካላትን ከማሳተፋቸውም በተጨማሪ ሰፊ የተለያዩ ልምዶች፣ ሀሳቦች እና ቀደም ሲል ከDCR ጋር የተሳትፎ ደረጃዎች ያሏቸው ነዋሪዎችን ሀሳብ መስጫያ እድሎችን ፈጥረዋል።

የተሳትፎ ሂደቱ ዋነኛ ዓላማ በታሪክ ውስጥ በDCR የህዝብ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶችና ስምሪት ላይ በዝቅተኛ ደረጃ የተወከሉ ነዋሪዎችና ማህበረሰቦችን ሀሳብ በቀጥታ መስማት ነበር። ግብረ ኃይሉ ከተደራሽነት፣ መሰረተ ልማት እና የመንገድ መዘጋቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው የግንኙነትና ስምሪት ችግሮችን፣ እና እንዴት DCR የበለጠ ውጤታማ በሆነ ትብብር፣ ቅንጅት እና የተሳትፎ እድሎች አማካኝነት ከማህበረሰቦች ጋር ጠንካራ ግንኙነቶችን መመስረት እንደሚችል ለመረዳት ሞክሯል።

ዋና ዋና ግኝቶች

በተሳትፎ ተግባሮቹ ወቅት በሙሉ የሚከተሉትን ጨምሮ የተለያዩ ጭብጦች ወጥነት ባለው መልኩ ተነስተዋል:

የበለጠ ወጥ የሆነ ግንኙነት አስፈላጊነት

ነዋሪዎች እንዴት DCRን እንደሚያናግሩ፣ ስለ ፕሮጀክቶችና የመንገድ መዘጋቶች በተመለከተ ከየት መረጃ እንደሚያገኙ፣ እና እንዴት ስጋቶች ወይም ጥያቄዎች እንደሚፈቱ በተመለከተ እርግጠኛ እንዳልሆኑ ገልጸዋል። የማህበረሰብ አባላት ወጥ በሆነ መልኩ ግልጽ ግንኙነት ማድረጊያ ቦታዎች፣ የበለጠ ቅድሚያ ግንኙነት እንዲኖሩ፣ እና በመደበኛነት የፕሮጀክት መረጃዎች እንዲሰጡ ጠይቀዋል።

የቅድመ እና የበለጠ ትርጉም ያለው ተሳትፎ አስፈላጊነት

ብዙ ተሳታፊዎች ስለ ፕሮጀክቶች በአብዛኛው የሚያውቁት ከዝግጅት ዙር ይልቅ በትግበራ ዙር ላይ እንደሆነ፣ ወይም ስለ ውሳኔዎች የሚያውቁት ከተወሰኑ በኋላ እንደሆነ ተናግረዋል። ነዋሪዎች ቅድሚያ ማስታወቂያዎችና ስምሪት፣ በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት በሙሉ ቀጣይነት ባለው መልኩ ወቅታዊ መረጃዎችን በማግኘት ለፕላኒንግ ሂደቶች ግብአት የሚሰጡባቸው እና በፕሮጀክቱ ወቅት በሙሉ የሚሳተፉባቸው ተጨማሪ እድሎች እንዲኖሩ ፍላጎታቸውን ገልጸዋል።

የእኩልና ተደራሽ ስምሪት አስፈላጊነት

ተሳታፊዎች መረጃ ለተለያዩ ማህበረሰቦች ተደራሽ በሆኑ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችና ፎርማቶች መቅረብ እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተዋል። የተሰጡት ጥቆማዎች በተለያየ ቋንቋ ስምሪትን፣ የታተሙ ጽሁፎችን፣ ማህበረሰብ ተኮር ስነምሪትን፣ መልዕክቶችና በአካል የሚሰጡ ማስታወቂያዎችን፣ እና ከተአማኒ ድርጅቶችና ተቋማት ጋር የሚደረጉ ትብብሮችን ያጠቃልላሉ።

የጠንካራ ቅንጅት አስፈላጊነት

የማህበረሰብ አባላት የDCR፣ የCambridge ከተማን፣ እና የሌሎች የህዝብ ድርጅቶችን የስራ ድርሻዎችና ኃላፊነቶች በተመለከተ ግራ መጋባት እንዳለ በተደጋጋሚ ገልፀዋል። ተሳታፊዎች በድርጅቶችና በከተማው መካከል ጠንካራ ቅንጅት እንዲኖር፣ እና የበለጠ ወጥ ለህዝብ መልዕክት ማስተላለፊያ እንዲኖር ፍላጎታቸውን ገልፀዋል።

የመሰረተ ልማትና ተደራሽነት ችግሮች

የማህበረሰብ አባላት በተጨማሪም በመንገዶች ትይዩና በማቋረጫዎች ላይ የእግረኞችና የብስክሌት ደህንነትን፣ እጽዋትና የመንገድ ጥገናን ጨምሮ የጥገና አስፈላጊነትን፣ ግልጽ ቅድሚያ የመጠምዘዣ መረጃን ጨምሮ የመንገድ መዘጋቶችን፣ እና አጠቃላይ የመንደር ተጽእኖዎችን ጨምሮ የተለያዩ ከመሰረተ ልማት ጋር ተያያዥ ችግሮች እንዳሉ ገልፀዋል። ምንም እንኳን እነዚህ ጉዳዮች ከግብረ ኃይሉ የመጀመሪያ ኃላፊነት አድማስ በላይ ቢሆኑም ግንኙነትን፣ ስምሪትን እና የህዝብ ተሳትፎ አሰራሮችን ለተመለከቱ ውይይቶች መረጃ ሰጥተዋል።

ምክረ ሀሳቦች

የተሳትፎ ሂደቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ ግብረ ኃይሉ ለDCR አራት ምክረ ሀሳቦችን አዘጋጅቷል።

ምክረ ሀሳብ 1: የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት ማሻሻያ

DCR ስለ ፕሮጀክቶች እና ኢኒሺየቲቮች መረጃ የሚገልጽበት ወጥ አቀራረብ ማዘጋጀት አለበት። ይህ ግልጽ የፕሮጀክት መረጃ፣ መደበኛ ወቅታዊ መረጃዎች መስጠትን፣ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን መጠቀምን፣ እና በፕሮጀክት ዝግጅትና ትግበራ ወቅት በሙሉ ለህዝብ ግብዓት መስጫ እድሎች መስጠትን ያካትታል።

ምክረ ሀሳብ 2: የአሰራር ሂደትና ግንኙነት ማሻሻያ

DCR የማህበረሰብ አባላትን እንዴት ከድርጅት ጋር እንደሚሳተፉ፣ መረጃ እንደሚያገኙ፣ ግብረ መልስ እንደሚሰጡ፣ እና እንዴት ወቅትን የጠበቁ ምላሾች እንደሚያገኙ እንዲረዱ የሚያግዙ ግልጽ የአሰራር ሂደቶችና የምላሽ ሰጪ ግንኙነት መሳሪያዎች ማዘጋጀት አለበት። ይህ ምክረ ሀሳብ የዕለት ከዕለት ግንኙነቶች ውጤታማነትን፣ ተጠያቂነትን እና ተደራሽነትን ማሻሻል ላይ ያተኩራል። DCR በኢኒሺየቲቮች ላይ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ትብብር በሚያደርግበት ወቅት የተሻሻለ አቀራረብና ዘዴዎችን መጠቀም እና እነዚህን ለአጋር ድርጅቶች ማጋራት አለበት።

ምክረ ሀሳብ 3: እኩልነትን እና ማህበራዊ ፍትህን ማማከል

DCR የተገለሉና በዝቅተኛ ደረጃ የተወከሉ ማህበረሰቦች በድርጅት ውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚሳተፉባቸው ትርጉም ያላቸው እድሎች ማግኘታቸውን የሚያረጋግጡ አሰራሮችን ማዘጋጀት አለበት። ይህ የአካባቢ ፍትህ መርሆዎችን፣ የቋንቋ ተደራሽነት ታሳቢዎችን እና የህዝብ ተሳትፎ ምርጥ አሰራሮችን ከፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ጋር ማቀናጀትን ያካትታል።

ምክረ ሀሳብ 4: በCharles ወንዝ ላይ የሙከራ ትግበራ ማካሄድ

DCR በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተገለጹ የግንኙነትና ተሳትፎ ስትራቴጂዎችን በLongfellow እና Eliot Bridges መካከል ባለው የCharles ወንዝ ኮሪደር ውስጥ በሚካሄዱ ፕሮጀክቶች፣ ፕሮግራሞችና ስራዎች ላይ መተግበር አለበት። ከዚህ የሙከራ ጥረት የሚገኘው ትምህርት በመላው ኮመንዌልዝ ውስጥ በህዝብ ተሳትፎ አሰራሮች ላይ ለሚደረጉ ሰፊ ማሻሻያዎች መረጃ በመስጠት ሊረዳ ይችላል።

አስቀድሞ መመልከት

ግብረ ኃይሉ የአንዳንዶቹ የእነዚህ ምክረ ሀሳቦች ትግበራ አሁን ባሉት ሰራተኞችና ሀብቶች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ሊተገበር እንደሚችል ይገነዘባል። ሆኖም ሌሎቹ ምክረ ሀሳቦች መተግበር ከመቻላቸው በፊት DCRን ሰራተኞችና የገንዘብ ድጋፍን ጨምሮ ከፍተኛ ሀብቶችን ይጠይቁታል። በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት ምክረ ሀሳቦች አሁን ባሉት ሀብቶች ሊደረጉ የሚችሉ ማሻሻያዎችን እና በግብረ ኃይሉ በታለመው መሰረት ትርጉም ያለውና ዘላቂ ተሳትፎን ለማሳካት የሚያስፈልጉ

ተጨማሪ ኢንቨስትመንቶችን በመለየት ለDCR ለድርጊት የተግባር ፍኖተ ካርታ ይሰጡታል። ይህን በማድረግ ምክረ ሀሳቦቹ ለህዝቡ ምን አካሄድ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚሳካ እና በረጅም ጊዜ ውስጥ ለአቅም ግንባታና የገንዘብ ድጋፍ ምን እንደሚያስፈልግ በተመለከተ ግልጽ ግንዛቤ ይሰጡታል።

2. መግቢያ

ከCharles Rive ትይዩ ካለው ቦታ ተደራሽነትና መጠቀም ጋር ተያያዥ ጉዳዮች ታሪካዊ ዐውድ

የአካባቢ ጥበቃና መዝናኛ መምሪያ ("DCR") ወደ ግማሽ ሚሊዮን ጋሻ የሚያክል መሬት የሚቆጣጠር መሆኑ በአገሪቱ ውስጥ ከትላልቆችና እጅግ ሰፊ የግዛት ፓርክ ሲስተሞች ውስጥ አንዱ ያደርገዋል። የኤጀንሲው ስራ የኮመንዌልዝ የተፈጥሮ፣ የባህልና የመዝናኛ ሀብቶቻችንን ለሁሉም ሰው ደህንነት በመጠበቅ፣ በማጎልበት እና በማሻሻል በሰዎችና በአካባቢ መካከል ያለውን ወሳኝ ግንኙነት በማጎልበት ላይ ያተኩራል።

የDCR መሰረተ ልማት ሰዎችን በእንከብካቤው ስር ካሉ ስነ ምህዳሮችና ተደራሽ የመዝናኛ አገልግሎት መስጫዎች ጋር ያገናኛቸዋል። የDCR ሰራተኞች ሁሉም ነዋሪዎችና ጎብኚዎች በግዛቱ ክፍት ቦታዎችና የህዝብ መሬቶች ውስጥ ሊዝናኑበት፣ የባለቤትነት ስሜታቸውን ሊገልጹበትና ሊያገኙበት የሚችሉበትን ጤናማና የበለጠ ለተፈጥሮ የማይበገር ማኅቹሴትስን ለመገንባት ይተጋሉ። DCR በታሪክ ውስጥ በመላው ግዛቱ ውስጥ የተገለሉ ማህበረሰቦችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማሳተፍ፣ ነዋሪዎችን ስለ ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች ለማሳወቅ የባከኑ እድሎችን ለመጠቀም፣ እና የማህበረሰብ ግብዓትን በቅድመ ውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ውስጥ ለማካተት ሲታገል ቆይቷል። እነዚህ ተግዳሮቶች DCR በCambridge ውስጥ በCharles ወንዝ ትይዩ ባለው ቦታ ላይ ከሚኖሩና ለቦታው ተደራሽ ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር በሚያደርገው ተሳትፎ ውስጥ ስር በሰደደ ሁኔታ አሉ።

ስለ Charles ወንዝ ግብረ ኃይል (CRTF)

የህግ አውጪ ህግ: ለFY2025 የፀደቀው በጀት ክፍል 205

የማሳቹሴትስ ሕግ አውጪ ለFY2025 በፀደቀው በጀት ክፍል 205 ("ክፍል 205") ስር የCharles ወንዝ ግብረ ኃይል ለዕኩል የወንዝ ተደራሽነትን ("CRTF" ወይም "ግብረ ኃይል") አቋቁሟል። ክፍል 205 የተደነገገው ለግብረ ኃይሉ በCambridge የወንዙ ጎን በኩል በLongfellow Bridge እና Eliot Bridge መካከል ያለው የCharles ወንዝ አካባቢን ዕኩል ተደራሽነት በተመለከተ ጥናት እንዲያደርግ እና ለDCR ምክረ ሀሳቦችን እንዲያዘጋጅ ኃላፊነት ለመስጠት ነው። CRTF: (i) DCR በLongfellow Bridge እና Eliot Bridge መካከል ያለውን የCharles ወንዝን ቦታ የተመለከቱ ውሳኔዎችን በሚያሳልፍበት ወቅት የአካባቢ ፍትህ መርሆዎችን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥን፣ (ii) Memorial Driveን መዝጋትን ወይም ተደራሽነትን መገደብን የተመለከቱ የፍሬ ጉዳይ ውሳኔዎች በሚተላለፉበት ወቅት ሁሉም ባለድርሻ አካላት መሳተፋቸውን ማረጋገጥን፣ (iii) የአነራባች መንደር ነዋሪዎች DCR በMemorial Drive ተደራሽነት ላይ ለውጦችን በሚያደርግበት ወቅት ተገቢ ማስታወቂያ ማግኘታቸውን ማረጋገጥን፣ እና (iv) ሰፊ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሊዝናኑባቸው የሚችሉ በCharles ወንዝ ትይዩ የሚካሄዱ ፕሮግራሞችን ማሻሻልን የሚያካትቱ ምክረ ሀሳቦችን እንዲያዘጋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

የክፍል 205 ዝርዝሮች በተጨማሪ ዝርዝር ሀ ውስጥ ተካተዋል።

የግብረ ኃይሉ አባላት

ክፍል 205 የCRTF አባላት የEEA የአካባቢ ፍትህ ምክትል ዋና ፀሀፊን፣ የDCR ኮሚሽነርን፣ የልዩ የማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮችን፣ እና ዋና መኖሪያቸው ከCharles ወንዝ በ1/2 ማይል ርቀት ውስጥ ከሆነና የአካባቢ ፍትህ ማህበረሰብ አባላት ከሆኑ ወይም ድንጋማ የሚሰጥበት መኖሪያ ቤት ነዋሪ ከሆኑ ነዋሪዎች ውስጥ ከ6 ያላነሱ ግለሰቦችን እንደሚያካትት እና ከግለሰቦቹ ውስጥ ቢያንስ 2ቱ የወንዝ ትይዩ መንደር ነዋሪ መሆን እንዳለባቸው ይገልጻል።

የግብረ ሀይሉ የጋራ ስብሳቢዎች እና አባላት በተጨማሪ ዝርዝር ለ ላይ ተዘርዝረዋል።

የፕሮጀክት ቡድን እና የጊዜ ሰሌዳ

የCRTF የፕሮጀክት ቡድን በጋራ የተመራው በማሳቹሴትስ የኢነርጂና የአካባቢ ጉዳዮች (EEA) ስራ አስፈጻሚ ጽህፈት ቤት እና በDCR ሲሆን ለፕሮጀክቱ እንደ አማካሪ በMetropolitan Area Planning Council (MAPC) ድጋፍ ተደርጎለታል። የEEA እና DCR ሰራተኞች ለግብረ ኃይሉ እንደ የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን ለግብረ ኃይሉ ስራ መረጃ ለመስጠትና ለመተግበር (ስዕል 1) እና የስራውን እድገት ለህዝብ ለመግለጽ አግዘዋል። MAPC የስብሰባ ማመቻቸት አቅርቧል፣ የህዝብ አስተያየቶችን ሰብስቧል እንዲሁም ለግብረ ኃይሉ በግኝቶቹና ምክረ ሀሳቦቹ ላይ የመጨረሻ ሪፖርቱን እንዲያዘጋጅ ድጋፍ አድርጓል።



ስዕል 1. *የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎች የጊዜ ሰሌዳ*

3. የCHARLES ወንዝ ግብረ ኃይል ተግባራት

የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎች

የCRTF ስብሰባዎች የትኩረት መስክ እና ውይይት

ከኦገስት 2025 እስከ ጁን 2026 ድረስ አስራ አንድ የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎች ተካሂደዋል። የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎች የተካሄዱት ለEEA፣ DCR፣ የግብረ ኃይሉ አባላት፣ እና ለMAPC ባለድርሻ አካል መለየትን፣ የተሳትፎና ስምሪት አሰራሮችን፣ ሰነዶችና ስትራቴጂን፣ የሪፖርት ምክረ ሀሳቦችን እና ሌሎችንም (ስዕል 2) ጨምሮ በሁሉም የፕሮጀክቱ ስራዎች ላይ የሚወያዩበት፣ ትብብር የሚያደርጉበት እና ውሳኔዎችን የሚያሳልፉበት ምህዳር ለመስጠት ነው። አጀንዳዎችና የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎችን ጨምሮ የግብረ ኃይሉ ስብሰባ ሰነዶች በCharles ወንዝ ግብረ ኃይል ድረገጽ፡ (https://www.mass.gov/info-details/charles-river-task-force-on-equitable-river-access#task-force-meetings) ላይ በይፋ ይገኛሉ።

TASK FORCE MEETING 1	Discussed: Project overview, scope of work, roles & responsibilities, timeline and the fall public hearing structure
TASK FORCE MEETING 2	• Discussed the history of the Charles River • Discussed goals of the task force and stakeholders • Reviewed the revised project timeline
TASK FORCE MEETING 3	• Discussed October and November engagement activities • Provided feedback on October Engagement activities • Confirmed details and discussed structure/content for November Public Hearings
TASK FORCE MEETING 4	Discussed recording task force meetings, site walk, and the structure and content of public hearings
TASK FORCE MEETING 5	Updated and discussed the public survey
TASK FORCE MEETING 6	• Task Force reflections of task force work so far. • Discussed feedback from fall public hearings engagement and survey • Discussed plan for task force work from January-June
TASK FORCE MEETING 7	Discussed spring focus group content and spring focus group outreach strategy and materials
TASK FORCE MEETING 8	• Reviewed Spring focus group flyer and discussed scheduling focus groups • Discussed public hearing outreach flyer • Discussed preliminary draft recommendations • Previewed draft public hearing agenda and survey
TASK FORCE MEETING 9	• Reviewed spring focus group outcomes and public hearing outreach flyer • Reviewed and discussed updated draft recommendations for public release • Reviewed and discussed draft survey
TASK FORCE MEETING 10	• Reviewed recommendations from public hearings, public hearing survey and focus group survey to date • Reviewed and discussed draft report
TASK FORCE MEETING 11	Discuss draft report
TASK FORCE MEETING 12	Vote on approving the final report

ስዕል 2. *የግብረ ኃይሉ ስብሰባዎች ማጠቃለያ*

የተሳትፎ እና ስምሪት ተግባሮች

የCRTF የተሳትፎ አሰራር የትኩረት ቡድኖችን፣ የአንድ ለአደንድ ውይይቶችን፣ የቤት ለቤት ስምሪትን፣ የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎችን፣ እና የህዝብ ዳሰሳ ጥናቶችን አካቷል። የተሳትፎ ተግባሮቹ የተዘጋጁት ሰፊ የተለያዩ የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላትን መድረሻና ግንኙነት ማድረጊያ አሰራሩን በማሻሻል ላይ ለEEA እና DCR ለሚሰጡ ምክረ ሀሳቦች መረጃ ለመስጠት እንዲረዱ ነው። የማህበረሰብ ተሳትፎን ማሻሻል በCambridge ውስጥ በLongfellow እና በEliot ድልድዮች መካከል ባለው በCharles ወንዝ ትይዩ በሚገኘው ቦታ ተደራሽነት እና መጠቀም ላይ ተጽእኖ ሊኖራቸው ለሚችሉ፣ ወይም በአጎራባች መንደሮችና ማህበረሰቦች ላይ ተጽእኖ ሊፈጥሩ ለሚችሉ የDCR ተግባሮች፣ እቅድ ዝግጅት፣ እና ውሳኔዎች ላይ አዎንታዊ ውጤት አለው። ከመኸር እስከ ፀደይ ወቅት የእነዚህ የተሳትፎ ተግባሮች ዋና ዋና ጭብጦችን ከተጨማሪ ዝርዝር መ ላይ ማግኘት ይቻላል።

የትኩረት ቡድኖች

በግብረ ኃይሉ በተመከሩና ስምምነት በተደረገባቸው ቦታዎች አራት የትኩረት ቡድን ውይይቶች ተካሂደዋል። የትኩረት ቡድን ውይይቶቹ ዓላማ የማህበረሰብ አባላትን ሀሳብ በቀጥታ መስማት ነበር። ከትኩረት ቡድኖቹ የተገኙት ጭብጦች ከDCR ጋር ግንኙነት የማድረግና የመረዳት ችግሮችን፣ ምን የስምሪት እና ተሳትፎ ዘዴዎች በጥሩ ሁኔታ ፍላጎቶቻቸውን እና ምርጫዎቻቸውን እንደሚያሟሉ፣ እና ከፓርኩ አገልግሎት መስጫዎች፣ ተደራሽነት እና ከጋራ የፓርክ መሬት አስተዳደር ጋር በተያያዘ በግንኙነት እና ስምሪት ጥረቶች ላይ በጠቅላላው DCR ምን ለውጦችን አድርጎ ማየት እንደሚፈልጉ አካተዋል። የትኩረት ቡድኑ ውይይት የተካሄደው በመኸር ወቅት በRivermark (808-812 Memorial Drive) ሲሆን ይህን ተከትሎም በፀደይ ወቅት ተጨማሪ ክፍለ ጊዜዎች በCambridge የመኖሪያ ቤት ባለስልጣን ህንጻዎች (Putnam Gardens and Woodrow Wilson Court) ውስጥ እና በCambridge Senior Center ውስጥ ተካሂደዋል።

የአንድ ለአንድ ውይይቶች

የአንድ ለአንድ ውይይቶች በመኸር ወቅት መጀመሪያ ላይ ስለ ማህበረሰቡ አውድ ጥልቅ ግንዛቤ ለማግኘት በCharles ወንዝ ትይዩ ያለውን ቦታ ለሚጠቀሙ ማህበረሰቦች ድጋፍ ከሚያደርጉ አራት የአካባቢ ድርጅቶች ሰራተኞች ጋር ተካሂደዋል። በአንድ ለአንድ ውይይቶቹ ላይ ተሳታፊ ድርጅቶች የተመረጡት በግብረ ኃይሉ ሲሆን የሚከተሉትን አካተዋል:

- የካምብሪጅ የማህበረሰብ ማዕከል (Cambridge Community Center: Zach Goldhammer)፣ የተሳትፎና ትብብር ዳይሬክተር
- Cambridgeport Neighborhood Association: Rebecca Bowie፣ አስተባባሪ
- የካምብሪጅ ከተማ (City of Cambridge): Jackson Price፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ ዳይሬክተር፤ Jeremy Warnick፣ የግንኙነቶች ዳይሬክተር
- Homeowners Rehab Inc.: Joe Deignan፣ የማህበረሰብ ተሳትፎ ዳይሬክተር

የቤት ለቤት ስምሪት

ስለ ኖቬምበር 2025 የመጀመሪያዎቹ ሁለት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎች መረጃ ለመስጠትና ለማጎልበት፣ እና ከማህበረሰብ አባላት ጋር በCharles ወንዝ ትይዩ ያለውን ቦታ አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ለመወያየት በመኸር ወቅት ሁለት የቤት ለቤት ስምሪት ጥረቶች ተካሂደዋል። የቤት ለቤት ስምሪቱ (ስዕል 3) ያተኮረው በCambridgeport እና Riverside መንደሮች ላይ ነበር። በጠቅላላው ከ35 ሰዎች ጋር ውይይቶች የተካሄዱ ሲሆን 129 በራሪ ጽሁፎች ተሰራጭተዋል።

የቤት ለቤት ስምሪቱ የተካሄደው በሚከተለው ነው:

- Putnam Avenue: ከPutnam Avenue እና Peabody Terrace ወደ ታች እስከ Putnam Avenue እና Pleasant Street ድረስ
- Western Avenue: ከWestern Avenue እና Memorial Drive ወደ ታች እስከ Western Avenue እና Howard Street ድረስ
- River Street: ከRiver Street እና Memorial Drive ወደ ታች እስከ River and Pleasant Street ድረስ




ስዕል 3. የቤት ለቤት ስምሪት ግባሮች ካርታ

የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎች

ስለ ግብረ ኃይሉ ስራ መረጃ ለመስጠት አራት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎች ተካሂደዋል። ሁለቱ የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎች የተካሄዱት በኖቬምበር 2025 ስለ የDCR ውሳኔዎች ተጽእኖዎች በተመለከተ የማህበረሰብ ግብዓት ለመሰብሰብሲሆን — አንደኛው የቨርቹዋል የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ በኖቬምበር 10 (55 ተሳታፊዎች ተሳትፈዋል) እና ሌላኛው የገጽ ለገጽ የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ በኖቬምበር 17 በCambridge የማህበረሰብ ማዕከል ተካሂዷል (77 ተሳታፊዎች ተሳትፈዋል)። ሁለት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎች በ2026 የፀደይ ወቅት የተካሄዱ ሲሆን — አንደኛው የገጽ ለገጽ የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ በኤፕሪል 29 በMorse Elementary School (21 ተሳታፊዎች ተሳትፈዋል) እና ሌላኛው የቨርቹዋል የህዘብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባ በሜይ 5 ተካሂዷል (24 ተሳታፊዎች ተሳትፈዋል)። የፀደይ ወቅት የህዝብ ሀሳብ መስሚያ ስብሰባዎቹ ዓላማ የግብረ ኃይሉን ረቂቅ ምክረ ሀሳቦች ዋና ዋና ሀሳብ መመልከት እና በምክረ ሀሳቦቹ እና ከእያንዳንዱ ምክረ ሀሳብ ጋር ተያያዥ በሆኑ የድርጊት ዝርዝሮች ላይ ግብረ መልስ መሰብሰብ ነበር። በፓርኩ፣ መንገዶች እና የመንገድ መስመሮች ላይ አካላዊ ለውጦችን ከማድረግ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጥያቄዎች ግብረ መልስ DCR እነዚህን ለብቻ የመዘገበ ሲሆን ግብረ መልሱን በወደፊት የካፒታልና ጥገና በጀት እቅድ ውስጥ ያካትታል።


የህዝብ ዳሰሳ ጥናቶች

ሁለት የአንላይን የህዝብ ዳሰሳ ጥናቶች የተካሄዱ ሲሆን አንደኛው በመኸር ወቅት እና ሌላኛው በፀደይ ወቅት ተካሂደዋል። የመኸር ወቅቱ የህዝብ ዳሰሳ ጥናት ከኦክቶበር 14 እስከ ዲሴምበር 31,2025 ተካሂዷል። በዚህ የዳሰሳ ጥናት በጠቅላላው 475 ምላሾች ተገኝተዋል። ከታች ስዕል 4 የዳሰሳ ጥናቱን ምላሽ ሰጪዎች ምድብ ያሳያል።



ስዕል 4. የመኸር ወቅት ዳሰሳ ጥናት ምላሽ ሰጪዎች ምድብ

ለመጨረሻው ሪፖርት በተለያዩ ምክረ ሀሳቦች ረቂቅ ላይ ግብረ መልስ በማግኘት ላይ ያተኮረው የፀደይ ወቅቱ የህዝብ ዳሰሳ ጥናት ከኤፕሪል 29 እስከ ሜይ 29 ድረስ ክፍት የነበር ሲሆን በጠቅላላው 232 ምላሾች ተገኝተውበታል። ከታች ስዕል 5 የዳሰሳ ጥናት ምላሽ ሰጪዎችን ምድብ ያሳያል። ለቀረቡት የዳሰሳ ጥናት ምላሾች ተጨማሪ ዝርዝር ሐን ይመልከቱ።



ስዕል 5. የፀደይ ወቅት ዳሰሳ ጥናት ምላሽ ሰጪዎች ምድብ


4. የዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ

ከመኸር ወቅት እና የፀደይ ወቅት የተሳትፎ ሰነዶች የተገኙ ዋና ዋና ጭብጦች


በጠቅላላ ግብረ መልስ፣ ሀሳቦች እና ስጋቶች ላይ ያተኮረው የመኸር ወቅት ተሳትፎ የሚከተሉትን ግልጽ አድርጓል:

- ለደህንነት አስተማማኝ የማቋረጫ መንገዶችን፣ የተሻሻለ የእግረኛ መንገድና የብስክሌት መንገድ ተደራሽነት እና መሰረተ ልማትን፣ ከፍተኛ ጥገናን ጨምሮ በፓርኩና የመንገድ መስመሩ ላይ ተጨማሪ የመሰረተ ልማት ማሻሻያዎች የማድረግ አስፈላጊነት።
- የመንገድ መስመሩ መዘጋት በማህበረሰቦች ላይ በተለያየ መልኩ ተጽእኖ መፍጠሩን የቀጠለ ሆኖ አንዳንድ የማህበረሰብ አባላት ስላገኟቸው ጥቅሞች ያረጋገጡ ሲሆን ሌሎቹ ስለሚፈጠሩባቸው ተጽእኖዎች በተመለከተ ስጋታቸውን ገልፀዋል፤ በተለይም ከመንገድ መስመሩ መዘጋት ጋር በተያያዘ በተወሰኑ ማህበረሰቦች ላይ ያልተመጣጠኑ ጫናዎች በሚያጋጥሙባቸው ቦታዎች።
- ለፕሮጀክቶች፣ ጥገና፣ ፕሮግራሞች እና የመንገድ መዘጋቶች ከDCR ተጨማሪ፣ ወጥ እና ቀጣይነት ያላቸው ግንኙነቶች እና ስምሪት አስፈላጊነት።

የሚከተሉት ስዕሎች 6-7 ከተለያዩ መድረኮች የተገኙ ዋና ዋና ጭብጦችን አጠቃለው ያቀርባሉ።



ስዕል 6. *ከመኸር ወቅት 2025 የተለያዩ የተሳትፎ ጥረቶች የተገኙ ጭብጦች*




***ስዕል** 7: ከ2025 የመኸር ወቅት የተሳትፎ መድረኮች የተገኙ ዋና ዋና አስተያየቶች ጭብጦች*


በግብረ ኃይሉ ምክረ ሀሳቦች የታቀደው ረቂቅ ላይ ግብረ መልስና ግብዓት መሰብሰብ ላይ ያተኮረው የፀደይ ወቅት ተሳትፎ የሚከተሉትን አሳውቋል:

- DCR በተለይም የDCR ፕሮጀክቶች ከሚካሄዱባቸው አካባቢዎች የአካባቢ ማህበረሰቦች ጋር የሚያደርጋቸው ተጨማሪ፣ ወጥ እና ቀጣይነት ያላቸው ስምሪት እና ግንኙነቶች አስፈላጊነት።
- ከማህበረሰብ አባላት ጋር ግንኙነት ለማድረግ እና መረጃ ለማጋራት የሚያስችሉ ዘዴዎችና አሰራሮችን የማጥናት እና ማስፋት አስፈላጊነት።
- አብዛኞቹ የተወሰዱት የህዝብ ግብዓቶችና ግብረ መልስ (ከትኩረት ቡድኖች እና የዳሰሳ ጥናት ምላሾች) ከታቀዱት የግብረ ኃይሉ ምክረ ሀሳቦች ጋር እንደሚስማሙ የተመለከተ ቢሆንም ነገር ግን ተጨማሪ ማብራሪያዎች እና የቋንቋ ግልጽነት (ለምሳሌ፡ ትርጓሜዎች፣ ልዩ መለኪያዎች፣ ግቦች፣ የጊዜ ሰሌዳዎች፣ ወዘተ) ያስፈልጋሉ።

የሚከተሉት ስዕሎች 8-11 በረቂቅ ምክረ ሀሳቦቹ ላይ የተሰጡትን ጠቅላላ አስተያየቶች (ከህዝብ ዳሰሳ ጥናት ምላሾች የተወሰዱ) አጠቃለው ያቀርባሉ:




ስዕል 8. *ለምክረ ሀሳብ 1 የተሰጡ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች*



ስዕል 9. *ለምክረ ሀሳብ 2 የተሰጡ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች*


Recommendation #3 - Centering Equity & Environmental Justice - *DCR to establish a clear process for ensuring marginalized communities and those who have historically been impacted by and excluded from public processes have a clear role in DCR processes*



ሰዕል 10. *ለምክረ ሀሳብ 3 የተሰጡ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች*

Recommendation #4 - Implementation

DCR to apply the communication and outreach recommendations above (Recommendations 1-3) to address physical infrastructure-related feedback received through this Task Force for the Charles River area between Longfellow and Eliot bridges, as a pilot for applying communication and outreach strategies for other DCR projects across the Commonwealth.



ሰዕል 11. *ለምክረ ሀሳብ 4 የተሰጡ የዳሰሳ ጥናት ምላሾች*

የሁለቱ የተሳትፎ ዙሮች ማረጋገጫ

CRTF በመጀመሪያ የፀደቀው በጁላይ 2024 እና ጁን 2025 መካከል እንደ የ6-ወራት ፕሮጀክት እንዲያጠናቅቅ ነበር። DCRን ባጋጠሙት የሰራተኛ አቅም ችግሮች እና የግብረ ኃይሉን ስራ ለመደገፍ የገንዘብ ድጋፍ ባለመገኘቱ ምክንያት ፕሮጀክቱን እስከ ጁላይ 2025 ድረስ መጀመር አልተቻለም ነበር። ፕሮጀክቱ አንዴ ከተጀመረ በኋላ በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎችን ሀሳቦች ለማግኘት የግብረ ኃይሉን ጠንካራ የተሳትፎ ዓላማዎች ከመፈጸም በተጨማሪ በፕሮጀክት ቡድኑ እና በግብረ ኃይሉ አባላት መካከል ግንኙነትን ለማጎልበት ከ6 ወራት በላይ እንዳስፈለገ የተረጋገጠ ነው። በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቱ በጁን 30,2026 እንዲጠናቀቅ ተራዝሟል።

በግብረ ኃይሉ የመጀመሪያ ስብሰባዎች ላይ ያጋጠሙትን መግባባትና ግንኙነትን የማጎልበት ችግሮች ለመፍታት እንዲረዳ በጃኑዋሪ 28, 2026 የተካሄደው የግብረ ኃይሉ ስብሰባ #6 የተዘጋጀ ሲሆን ስብሰባው የተዘጋጀው እስከ ፀደይ ወቅት ድረስ በግብረ ኃይሉ ስራ እና ተሳትፎ ለመቀጠል የሚያስችሉ ተመራጭ መንገዶችን ለመወሰን፣ እና የመጨረሻውን ሪፖርት ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ ክፍሎችን ለመወሰን እንደ ረጅም የገጽ ለገጽ ስብሰባ ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ የDCR ኮሚሽነር እና የኢነርጂና የአካባቢ ጉዳዮች የአካባቢ ፍትህ ምክትል ዋና ፀሀፊ በCRTF ስብሰባዎች እና ተግባራት ላይ በንቃት ከመሳተፋቸውም በተጨማሪ በአመራር ተሳትፎ እና በተሳትፎ ላይ የግብረ ኃይሉን ፍላጎት ገልፀዋል።

ለDCR የግብረ ኃይሉን ምክረ ሀሳቦች እንዲተገብር ድጋፍ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የፋይናንስ ሀብቶች እና የሰራተኛ አቅም

DCR በዚህ ሂደት ወቅት በተሰበሰበው ግብረ መልስ አማካኝነት ከማህበረሰቦች ጋር የሚደረጉ የግንኙነት ጥረቶችን እና የስምሪት ዘዴዎችን የማጠናከር አስፈላጊነትን ተገንዝቧል። በቅርብ ዓመታት ውስጥ እንደ ከነዋሪዎች ለሚነሱ ጥያቄዎችና ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ የማህበረሰብ ግንኙነቶች ቡድን መቋቋምን ከማዘጋጃ ቤቶች፣ ተመራጭ ኃላፊዎች እና በDCR በሚተዳደሩ ንብረቶችና ሀብቶች ላይ ጥቅም ካላቸው የአካባቢ የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር ትብብር የሚያደርግ የትብብር ቡድን መቋቋምን የመሳሰሉ የተለያዩ ማሻሻያዎች ተተግብረዋል። DCR በተጨማሪም የህዝብ ተሳትፎ ዳይሬክተር ያለው ከመሆኑም በተጨማሪ በቅርቡ የአካባቢ ፍትህ ከፍተኛ ዳይሬክተር ቀጥሯል። የአቅም ውሱንነቶች አሁንም DCR ወይም ግብረ ኃይሉ ለዚህ ልዩ ቦታ እና በተለይም በመላው ግዛቱ ውስጥ ባለሙት መልኩ በDCR የተሳትፎ ግቦቹን የማሳካት ችሎታ ላይ ተጽእኖ እየፈጠሩ ነው። ከዚህ በታች የተገለጹት የምክረ ሀሳቦቹ የትግበራ ስትራቴጂዎች እና የጊዜ ሰሌዳ ክፍሎች እነዚህን ወደፊት ለማስቀጠል ምን እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ።

5. የCRTF ገለጻዎች

ግብረ ኃይሉ በስራው ወቅት ውስጥ በሙሉ ወደፊት በDCR እና በሌሎች ድርጅቶች ለሚካሄዱ የማህበረሰብ ተሳትፎ ጥረቶች፣ ለአማካሪ አካላት፣ እና ለህዝብ ተሳትፎ የአሰራር ሂደቶች መረጃ በመስጠት ሊረዱ የሚችሉ የተለያዩ ትምህርቶችን አግኝቷል።

የፕሮጀክት ዲዛይን እና የጋራ መግባቢያ

ግብረ ኃይሉ ስለ ፕሮጀክቱ ዓላማዎች፣ አድማስ፣ የህግ ሀሳብ እና የሚጠበቁ ውጤቶች በተመለከተ ከመነሻው የጋራ መግባቢያ ላይ መድረስ ስኬታማ ለመሆን አስፈላጊ እንደሆነ ተገንዝቧል። የግብረ ኃይሉን ኃላፊነት እና ዓላማዎች በተመለከተ የተፈጠረው ቅድሚያ ጥርጣሬ ለተሳታፊዎች የተለያዩ የሚጠበቁ ሁኔታዎች አስተዋጽኦ ከማድረጉም በተጨማሪ በፕሮጀክቱ አካሄድ ላይ ተጽእኖ ፈጥሯል። የወደፊት ጥረቶች ከሚከተሉት ይጠቀማሉ፡-

- ግቦችን፣ የስራ ድርሻዎችን፣ ኃላፊነቶችን፣ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን፣ እና የሚጠበቁ ውጤቶችን በግልጽ የሚገልጽ አጠቃላይ የፕሮጀክት ማስጀመሪያ፤
- ዋና ዋና መለኪያዎችን፣ አቅርቦቶችን፣ የውሳኔ ነጥቦችን፣ እና የተሳታፊ ግብዓት ዕድሎችን የሚገልጽ የጋራ የፕሮጀክት ዕቅድ፤
- ወደ ጥረት ምስረታ የሚመራ በህግ እና ታሪካዊ ዐውድ ላይ የሚሰጥ ቅድሚያ ማብራሪያ፤ እና
- ስለ ማህበረሰብ ሁኔታዎችና የአካባቢ እይታዎች የጋራ መግባባትን ለማጎልበት የሚያስችሉ የሳይት ጉብኝቶችና ቦታን መሰረት ያደረጉ የትምህርት ዕድሎች።

የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ውክልና

በሂደቱ ውስጥ በሙሉ ዋናው ተግዳሮት የነበረው በህግ በተሰጠው ኃላፊነት እና በህዝብ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ በታሪክ ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ በተወከሉ ማህበረሰቦች ፍላጎቶች ላይ ትኩረት ከማድረግ ጎን ለጎን በግብረ ኃይሉ አባላት እና በማህበረሰብ ተሳታፊዎች የተነሱትን ሰፊ የተለያዩ ሀሳቦች ማመጣጠን ነበር። ግብረ ኃይሉ የሚከተለውን ተገንዝቧል:

- በታሪክ ሂደት ከDCR ጋር ተሳታፊ ካልነበሩ ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነቶችን መፍጠር ከፍተኛ ጊዜ እና የታሰበበት ስምሪት ማድረግን እንደሚፈልግ፤
- ከቀዳሚ ፕሮጀክቶችና ውሳኔዎች የመጣው አሁን ያለው እምነት ማጣት በተሳትፎ እና የማህበረሰብ አመለካከቶች ላይ ተጽእኖ ሊፈጥር እንደሚችል፤
- DCR በአብዛኛው ከኤጀንሲው ጋር መሰረት የያዙ ግንኙነቶች ባላቸው ድርጅቶችና ባለድርሻ አካላት ላይ እምነት መጣሉ አዲስ ድምጾችን ለመድረስ እንቅፋት እንደሚፈጥር፤ እና
- የተሳትፎ ሂደቶቹ በታሪክ ሂደት በዝቅተኛ ደረጃ የተወከሉ ማህበረሰቦችን ትርጉም ባለው መልኩ ከማካተት ጎን ለጎን ሰፊ የህዝብ ተሳትፎ እድሎችን መስጠቱን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥረት እንደሚያስፈልግ።

አቅም፣ ሀብቶች እና የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነት

ግብረ ኃይሉ ትርጉም ያለው ተሳትፎ ከፍተኛ የጊዜ፣ የሰራተኞች፣ የገንዘብ ድጋፍ እና የድርጅታዊ አቅም ኢንቨስትመንት እንደሚፈልግ ተገንዝቧል። የሀብት ውሱንነቶች የቤት ለቤት ስምሪትን፣ በራሪ ጽሁፎችን ማሰራጨትን፣ እና የግንኙነት ፈጠራ ጥረቶችን ጨምሮ በስምሪት ተግባራቱ አድማስ ላይ ተጽእኖ ፈጥረዋል። ግብረ ኃይሉ በተጨማሪም የሚከተሉትን ተገንዝቧል፡

- የተለያዩ ተሞክሮዎችና ፍላጎቶችን በሚወክል ትልቅ መካከል ዘላቂ ተሳትፎና የጋራ ስምምነትን ማጎልበት በተለይም በተራዘመ የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳ ላይ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል፤

- የፕሮጀክት ቡድኖች የትብብር የተሳትፎ ሂደቶችን ለማመቻቸትና ውስብስብ የባለድርሻ አካል ተለዋዋጭ ፍላጎትን ለመጠቀም ከስልጠና ድጋፍና ተለዋዋጭነት ተጠቃሚ እንደሚሆኑ፤ እና
- ጠንካራ የማህበረሰብ ተሳትፎ በአንድ ብቻ ኢኒሺየቲቭ ሊሳካ እንደማይችል እና ከዚህ ይልቅ በጊዜ ሂደት ዘላቂ ተቋማዊ ቁርጠኝነት እና ኢንቨስትመንት እንደሚፈልግ።

ዋና ዋና ምልከታዎች

በዚህ ሪፖርት ውስጥ ከተካተቱት ምክረ ሀሳቦች በተጨማሪ ግብረ ኃይሉ ከCharles ወንዝ ኮሪደር ትይዩ ከመሰረተ ልማት፣ ተደራሽነት፣ ጥገናና ደህንነት ጋር በተያያዘ የማህበረሰብ ስጋቶችን መዝግቧል። ምንም እንኳን እነዚህ ጉዳዮች ከግብረ ኃይሉ የመጀመሪያ ኃላፊነት አድማስ በላይ ቢሆኑም በDCR እና በሚያገለግላቸው ማህበረሰቦች መካከል የሚደረግ ቀጣይነት ያለው ግንኙነት፣ ተሳትፎና ትብብር አስፈላጊነትን ያሳንሱታል።

6. የመጨረሻ የCRTF ምክረ ሀሳቦች

DCR ከግብረ ኃይሉ ጋር በጋራ በሰራበት ወቅት በተገኘው ግብረ መልስ አማካኝነት በDCR ጥበቃ ስር ባሉ የፓርክ መሬቶች ዙሪያ ካሉ ማህበረሰቦች ጋር የሚደረጉ የተሳትፎ ጥረቶችን በተጨባጭ ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ተገንዝቧል። ከዚህ በተጨማሪም DCR እና ሌሎች የግዛትና የማዘጋጃ ቤት ድርጅቶች የግንኙነት፣ እቅድ ዝግጅት እና የስምሪት ዘዴዎችን ለማሻሻል በቅንነት መስራት ይኖርባቸዋል።

የቀረቡት እያንዳንዱ የሚከተሉት አራት (4) ምክረ ሀሳቦች የDCRን የግንኙነት እና ስምሪት አሰራሮችን ለማሻሻል የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይገልጻሉ። ለእያንዳንዱ እነዚህ ምክረ ሀሳቦች ግብረ ኃይሉ በተጨማሪም የልዩ የትግበራ ስትራቴጂዎች ወይም ድርጊቶች ጥቆማ ሰጥቷል፣ ከDCR እና EEA በተገኘው መመሪያ ላይ ተመስርቶ የጊዜ ሰሌዳ ዕቅድ አቅርቧል እንዲሁም DCR እነዚህን ለመተግበር በቂ ሀብቶችና ድጋፍ ያሉት መሆኑን ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆኑ ሀብቶችን ጠቁሟል። ለDCR ለአንዳንዶቹ እነዚህ ምክረ ሀሳቦች ትግበራ ድጋፍ ለማድረግ ተጨማሪ የገንዘብ ሀብቶች እና የሰራተኛ አቅም ያስፈልጋል።

<u>ምክረ ሀሳብ 1 – የፕሮጀክት ዕቅድ ዝግጅት ማሻሻያ:</u> DCR በአጭር እና በረጅም ጊዜ የታቀዱ ፕሮጀክቶችን የሚገልጽበት ግልጽ እና ወጥ አሰራር ያዘጋጃል።

የመነሻ ዐውድ: *ይህ ምክረ ሀሳብ የተዘጋጀው የፕሮጀክት ሰራውን ተጽእኖ በተፈጠረበት የፕሮጀክቱ ቦታ ላይ ለሚኖሩ የማህበረሰብ አባላት ለመግለጽ የበለጠ መደበኛና ወጥ አቀራረቦች መኖር አሰፈላጊነትን መሰረት አድርጎ ነው። ግብረ ሀይሉ ከማህበረሰቡ የሰማው ወጥነት ያለው ጭብጥ ከDCR በፕሮጀክት አካሄድ እና ቀጣይ ደረጃዎች ላይ ተጨማሪ መደበኛ ወቅታዊ መረጃዎችን የማግኘት ፍላጎት ነው። በአሁኑ ወቅት ያሉት የማህበረሰብ አባላት በማንኛውም የተወሰነ ጉዳይ ላይ ለDCR አስተያየቶችን መስጠት ወይም ሲጋቶችን ማጋራት የሚችሉባቸው የአሰራር ዘዴዎች ውሱን ናቸው። ይህ ምክረ ሀሳብ DCR እንዴት ከማህበረሰብ አባላት ጋር ግንኙነት እንደሚያደርግ እና ወቅታዊ መረጃዎችን እንደሚሰጥ በተመለከተ የበለጠ ወጥ አሰራሮችን እንዲያከናውን ለማስቻል የታሰበ ነው።*

የጊዜ ሰሌዳ ፍቺዎች: የአጭር ጊዜ = ከ3 ወራት-2 ዓመታት፣ የመካከለኛ ጊዜ = ከ3-5 ዓመታት፣ የረጅም ጊዜ = >5 ዓመታት።

ሌሎች ፍቺዎች: CRM = የደንበኛ ግንኙነት አስተዳደር

የተመከሩ የትግበራ ስትራቴጂዎች ወይም ድርጊቶች	የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ	ትግበራውን ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ሀብቶች	ተግባራዊ የተደረገ ወይም በሂደት ላይ ያለ
1. ተጽእኖ ሊፈጠርባቸው ከሚችል ማህበረሰቦች ጋር ስለ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች (የዕቅድ ዝግጅት፣ የተለያዩ ዙሮች እና ወቅታዊ መረጃዎች) በተመለከተ የበለጠ ውጤታማ በሆነ መልኩ ግንኙነት ለማድረግ የሚያስችሉ የባለድርሻ አካል አስተዳደር ቴክኖሎጂ እና የአሰራር ሂደቶችን መተግበር። የግንኙነት / መልዕክት ተቀባዮች የማህበረሰብ መሪዎች/ቡድኖችን፣ የአካባቢ አብያተ ክርስትያናትን፣ የባህል ማዕከሎችን፣ የአረጋውያን ማዕከሎችን፣ ከአካባቢ ማዘጋጃ ቤቶች እና አጋር የግዛት ድርጅቶች በተጨማሪ የአረጋውያን ቤቶች፣ የህዝብ እና በተመጣጣኝ ዋጋ የሚቀርቡ ቤቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ።	የአጭር ጊዜ	**ሰራተኞች:** ነባር ሰራተኞች **IT:** በትግበራ ሂደት ላይ ያለ የCRM መሳሪያ **ሌሎች ሀብቶች:** የሉም	የDCR የህዝብ ጉዳዮች ቡድን በአሁኑ ወቅት የጉዳይ አስተዳደር መሳሪያን የሚጠቀም ሲሆን ይህም ማስታወሻዎችን ለማደራጀት ጠቃሚ ቢሆንም ነገር ግን ለማህበረሰብና አጋሮች ስምሪት አይነት፣ ትብብር እና DCR ለማካሄድ ለሚፈልገው ግንኙነት ስራ ብዙ ሌሎች ጉዳዮች ይጎድሉታል።
2. ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የፕሮጀክት ግቦችን፣ የሚታሰቡ አማራጮችን፣ የታቀዱ ውጤቶችን፣ የማህበረሰብ ግብዓት ማግኛ እድሎችን፣ እና የፕሮጀክት ወቅታዊ መረጃዎችን የሚገልጹ ወደ ውጭ የሚመለከቱ የፕሮጀክት ማረፊያ ቦታ ገጾች ማዘጋጀት - ለምሳሌ፡ እንደ የCambridge	የአጭር ጊዜ ወይም የመካከለኛ ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ለግንኙነቶች ቡድን የአይቲ መሰረተ ልማትን ለማስተዳደር ተጨማሪ ድጋፍ የሚሰጡ እና ለህዝብ ጉዳዮች የበለጠ ተደጋጋሚ የፕሮጀክት ወቅታዊ መረጃዎች እንዲሰጥ ተጨማሪ ድጋፍ	DCR በአሁኑ ወቅት ለብዙ ትላልቅ እና ባለ ብዙ ዙር ፕሮጀክቶች የፕሮጀክት ድረገጾችን የሚያዘጋጅ ሲሆን እነዚህን ድረገጾች የፕሮጀክት መረጃና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመለጠፍ ይጠቀምባቸዋል። DCR በmass.gov ድረገጽ ሲስተም ላይ

የተመከሩ የትግበራ ስትራቴጂዎች ወይም ድርጊቶች	የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ	ትግበራውን ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ሀብቶች	ተግባራዊ የተደረገ ወይም በሂደት ላይ ያለ
ከተማ የግንባታ ፕሮጀክቶች ድረገጽ የተለመደ አገልግሎት ባለው ፎርማት።		የሚሰጡ። **IT:** በመልማት ላይ ያለ የፕሮጀክት አስተዳደር ሲስተም (የውስጥ)፤ ነባር ወደ ውጭ የሚመለከት አይቲ **ሌሎች ሀብቶች:** የሉም	ሊደረጉ ስለሚችሉ ማሻሻያዎች እያሰበ ነው።
3. በፕሮጀክት ልማቶች እጅግ ተጽእኖ ሊፈጠርባቸው ለሚችል ማህበረሰቦች የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ወጥ የግንኙነት አቀራረብ ማዘጋጀት። ለምሳሌ፡ ወቅታዊ መረጃዎች በሚሰጡበት አካላዊ ቦታ በቅርበት ከፕሮጀክቱ አስቀድሞ የሚለጠፉ በራሪ ጽሁፎችን ማካተት እና እንደ ጋዜጦች፣ የራዲዮ ወይም የአካባቢ ቲቪ ማሰራጫዎችን መጠቀም፣ እንዲሁም ከአንድ በላይ ቋንቋዎች የሚጠቀሙ ማሰራጫዎችን ዒላማ ያደረጉ የማህበራዊ ትስስር ገጾችን መጠቀም።	የመካከለኛ ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች ቡድን የተሻሻሉ የስምሪት እና የተሳትፎ ተግባሮችን እንዲተገብር ተጨማሪ ድጋፍ የሚያቀርቡ። **IT:** የCRM መሳሪያ በትግበራ ሂደት ላይ ነው **ሌሎች ሀብቶች:** የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶች፣ የፖስታና የሚዲያ ግዢዎች የገንዘብ ድጋፍ፣ ወዘተ።	DCR በአሁኑ ወቅት በህግ አውጪ፣ የማዘጋጃ ቤት እና የታወቀ ባለድርሻ አካል ገለጻዎች አማካኝነት የህዝብ ስብሰባዎችን እያነለበት ከመሆኑም በተጨማሪ እነዚህን በየኔትወርኮቻቸው የህዝብ ስብሰባዎች ግንዛቤን እንዲያሰራጩ ያበረታታል። DCR በተጨማሪም የህዝብ ስብሰባዎች ድረገጹን ያዘምናል እንዲሁም ስለ እነዚህ ስብሰባዎች በተመለከተ የስምሪት ኢሜይሎችን ይልካል።
4. ዕኩል የመረጃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ። የዚህ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ: ○ በግልጽ ቋንቋ የተጻፉ ጽሁፎችን እና ማጠቃለያዎችን መጠቀም ○ ተደራሽ ፎርማቶችን እና ወጥ ዲዛይን መጠቀም ○ ሰነዶችን መተርጎም	የአጭር ጊዜ	**ሰራተኞች:** ነባር ሰራተኞች **IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:** የቋንቋ ተደራሽት አገልግሎቶች	DCR በአሁኑ ወቅት ሁሉንም የህዝብ ስብሰባ ማስታወቂያዎች ወደ አምስት ዋና ዋና በማሳቹሴትስ ውስጥ በአብዛኛው የሚነገሩ ቋንቋዎች ያስተረጉማል። DCR በተጨማሪም በኦንላይን ላይ ለተመሰረቱ ሰነዶች የዲጂታል ተደራሽነትን በተመለከተ ከፍተኛ እድገት እያመጣ ነው።

<u>ምክረ ሀሳብ 2 – የአሰራር እና የግንኙነት ማሻሻያ:</u> DCR በተለይም በመካሄድ ላይ ያሉ እና/ወይም በቀጣይ የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ባሉባቸው ቦታዎች ላይ የማህበረሰቡን ፍላጎቶች ለመፍታት ግልጽ አሰራሮች እና የመከላከያና ምላሽ መስጫ መሳሪያዎችን ያብራራል እንዲሁም ያዘጋጃል።

የመነሻ ዐውድ: *በአሁኑ ወቅት አባላት በአብዛኛው ግብረ መልስ እና/ወይም ስጋቶች ሲኖሯቸው በDCR እንዴት እና/ወይም ማንን ማናገር እንዳለባቸው ግራ እየተጋቡ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የማህበረሰብ አባላት ከDCR ወጥ የግንኙነት ወቅታዊ መረጃዎች አይደርሷቸውም፣ ተገቢ ምላሾች አይሰጧቸውም ወይም ከትትል አይደረግላቸውም። የዚህ ምክረ ሀሳብ ዓላማ DCR ተጨማሪ የግንኙነት እና የማስተባበሪያ አሰራር ዘዴዎችን እንዲያካትት ለማድረግ ነው።*

የጊዜ ሰሌዳ ፍቺዎች: የአጭር ጊዜ = ከ3 ወራት-2 ዓመታት፣ የመካከለኛ ጊዜ = ከ3-5 ዓመታት፣ የረጅም ጊዜ = >5 ዓመታት።

ሌሎች ፍቺዎች: CRM = የደንበኛ ግንኙነት አስተዳደር

የተመከሩ የትግበራ ስትራቴጂዎች ወይም ድርጊቶች	**የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ**	**ትግበራውን ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ሀብቶች**	**ተግባራዊ የተደረገ ወይም በሂደት ላይ ያለ**
1. ለማህበረሰብ አባላት ፕሮጀክቶችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ወይም በፓርኩና የመንገድ መስመሩ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥሩ የመንገድ መዘጋቶችን ለተመለከቱ ጥያቄዎች የሚሄዱበት የግንኙነት ቦታ ማቅረብ።	የረጅም ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የጠመሰረተ)፣ በDCR የስራ ክፍሎች ውስጥ የሚመደብበትን ቦታ ለመወሰን ከሚያስፈልግ ተጨማሪ ስትራቴጂያዊ የዕቅድ ዝግጅት ጋር	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች ከፍተኛ የDCR ንብረቶች ላሉባቸው ቦታዎች የተመደቡ የማህበረሰብ ግንኙነቶችን እንዲያቋቁም ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርጉ **IT: የ**CRM መሳሪያ በትግበራ ሂደት ላይ ነው **ሌሎች ሀብቶች:** የሉም	ለትላልቅ የDCR ፕሮጀክቶች የግንኙነት ቦታ በአብዛኛው በፕሮጀክቱ ድረገጽ ላይ ይለጠፋል።
2. ስለ DCR የማህበረሰብ ግንኙነቶች ቡድን እና የማህበረሰብ አባላት እንዴት DCRን መድረስ እንደሚችሉ፣ ምን አይነት ጥያቄዎች ወዴት መሄድ እንዳለባቸው፣ እና ምን የምላሽ መስጫ የጊዜ ሰሌዳ ሊጠብቁ እንደሚችሉ የተመለከቱ ሌሎች የህዝብ ግብዓት አሰራሮችን ለማሳወቅ የመረጃ መስጫ ዘመቻ ማስጀመር።	የአጭር ጊዜ	**ሰራተኞች:** ነባር ሰራተኞች **IT:** ነባር አይቲ **ሌሎች ሀብቶች:** የግንኙነት ሰነዶች፣ የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶች	በአሁኑ ወቅት ህዝቡ DCRን በስልክ ቁጥር (617) 626-1250 ወይም በ፡ mass.parks@mass.gov ማግኘት ይችላል። በተጨማሪም ህዝቡ ግብዓት ማስገቢያ እድሎችን ለማየት የDCRን <u>የህዝብ ስብሰባ ድረገጽ</u> እና <u>የህዝብ አስተያየቶች ፖርታል</u> መጠቀም ይችላል።

3. ነዋሪዎች ስጋቶቻቸው እንዴት ከግምት ውስጥ እንደገቡ ወይም እንደተፈቱ ክትትል ማግኘት እንዲችሉ ከፕሮጀክት ጋር ተያያዥ የግንኙነት ግብረ መልስ መስጫ እድሎችን ማጠናከር።	የመካከለኛ ጊዜ	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች የግብረ መልስ መስጫ እድሎች ወጥ፣ ምላሽ ሰጪ እንደሆኑ፣ እና በወቅቱ እንደሚቀርቡ እንዲያረጋግጥ ተጨማሪ ድጋፍ የሚደርጉ። **IT:** የCRM መሳሪያ በትግበራ ሂደት ላይ ነው **ሌሎች ሀብቶች:** የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶች	ለDCR የሚደረጉ ጥሪዎች በአብዛኛው በዛው ቅጽበት መፍትሄ ያገኛሉ ወይም ለነዋሪው ተገቢ ክትትል ይካሄዳል። በህዝብ ስብሰባዎች ወቅት ለሚሰጡ አስተያየቶች በዛው ቅጽበት ወይም ከዚያ በኋላ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፍትሄ ለመስጠት ይሞከራል።
4. ስለ የመንገድ መዘጋቶች፣ መቋረጦች እና የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳዎች በተመለከተ ቅድሚያ ማስታወቂያ እና ግልጽ ማብራሪያዎች መስጠት።	የአጭር ጊዜ	**ሰራተኞች:** ነባር ሰራተኞች **IT:** የCRM መሳሪያ በትግበራ ሂደት ላይ ነው **ሌሎች ሀብቶች:** የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶች	DCR በአሁኑ ወቅት ማስጠንቀቂያዎችን ለDCR ወቅታዊ መረጃዎች ለተመዘገበ ለማንኛውም ሰው በኢሜይል የሚልክ ከመሆኑም በተጨማሪ በ፡ DCR የፓርክ ማስጠንቀቂያዎች ድረገጽ ላይ ይለጥፋል።
5. የስምሪት ጥረቶችን ተጽእኖ ለተፈጠረባቸው ማህበረሰቦች ለማስተባበርና አጉልቶ ለማሳየት በማዘጋጃ ቤቶችና የግዛት ድርጅቶች ውስጥ ካሉ ዋና ዋና መምሪያዎችና የግንኙነት ቡድኖች ጋር የሚደረግ ትብብርን ማሻሻል እና ማሳደግ።	የረጅም ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች ከማዘጋጃ ቤት እና የግዛት ድርጅቶች ጋር የሚያደርገውን ትብብር እንዲያሻሽል ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርጉ። **IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:** የማዘጋጃ ቤት እና የግዛት ኤጀንሲ ትብብር እና ከDCR ጋር ግንኙነት የማድረግና የመተባበር አቅም	DCR በአሁኑ ወቅት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ህግ አውጪዎች፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ እህት ድርጅቶች እና አጋሮች ጋር ግዛት አቀፍ ግንኙነት የማድረግ ኃላፊነት የተሰጣቸው 5 አስተባባሪዎችን የያዘ ቡድን አለው።

ምክረ ሀሳብ 3 – ዕኩልነትን እና የአካባቢ ፍትህን ማዕከል ማድረግ: DCR የተገለሉ ማህበረሰቦች እና በታሪክ ተጽእኖ የተፈጠረባቸውና የተገለሉ አካላት በDCR አሰራሮች ውስጥ ግልጽ ሚና እንደሚኖራቸው የሚያረጋግጥ ግልጽ አሰራር ያዘጋጃል።

መነሻ ዐውድ: የማህበረሰብ አባላት በብዙ ሁኔታዎች በDCR የሚተላለፍ ውሳኔ የቅርብ ተጽእኖ የሚፈጠርበትን ማህበረሰብ ድምጽ እንደማይገልጽ ወይም እንደማያካትት ይገልጻሉ። የማህበረሰብ አባላት በዕቅድ ዝግጅትና የውሳኔ አሰጣጥ መለኪያዎች ውስጥ እንደተካተቱ ስለማይሰማቸው በውጤቶቹ ከመደሰት ይልቅ በአብዛኛው መዘዝ ይተርፋቸዋል (ለምሳሌ፡ የትራፊክ መጨናነቅ፣ ከደህንነት ጋር ተያያዥ ችግሮች፣ ወዘተ)። ግብረ ሀይሉ ይህ ምክረ ሀሳብ በሁሉም የDCR የእቅድ ዝግጅትና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ላይ ዕኩልነትን እንደሚያረጋግጥ ያምናል።

የጊዜ ሰሌዳ ፍቺዎች: የአጭር ጊዜ = ከ3 ወራት-2 ዓመታት፣ የመካከለኛ ጊዜ = ከ3-5 ዓመታት፣ የረጅም ጊዜ = >5 ዓመታት።

ሌሎች ፍቺዎች: CRM = የደንበኛ ግንኙነት አስተዳደር

የተመከሩ የትግበራ ስትራቴጂዎች ወይም ድርጊቶች	**የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ**	**ትግበራውን ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ሀብቶች**	**ተግባራዊ የተደረገ ወይም በሂደት ላይ ያለ**
1. እንደ የፕሮጀክት ቅድመ-ዕቅድ ዝግጅት ዙር ክፍል ማን በግንባታው ወይም በመጨረሻ የፕሮጀክት ውጤቶች ተጽእኖ ሊፈጠርበት እንደሚችል ለመወሰን እና እነዚህ በዚህ ፕሮጀክት የቆይታ ዘመን ውስጥ በሙሉ ምን ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ወይም እንዳለባቸው ለመወሰን በየትኛውም ፕሮጀክት መጀመሪያ ላይ ሂደቶችን ማከናወን።	የአጭር ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች ቡድን ተጽእኖ የሚፈጠርባቸው ማህበረሰቦችን እንዲያጠናና ጠንካራ የስምሪት ዕቅዶችን እንዲያዘጋጅና እንዲተገብር ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርጉ። **IT:** የCRM መሳሪያ በትግበራ ሂደት ላይ ነው **ሌሎች ሀብቶች:** በሀሳብ ማመንጫ ዙር ላይ የፕሮጀክት ተጽእኖ ጥናቶችን የሚያዘጋጁ አማካሪዎች።	ለአብዛኞቹ ፕሮጀክቶች በቅድመ-ዕቅድ ዝግጅት/የዲዛይን ዙሮች ወቅት DCR ከሰፊ የህዝብ ስብሰባዎች አስቀድሞ የህግ አውጪ፣ የማዘጋጃ ቤት እና የታወቀ ባለድርሻ አካል ገለጻዎችን ያካሂዳል።
2. እንደ የፕሮጀክት ቅድመ-ዕቅድ ዝግጅት ዙር ክፍል ተለይተው በታወቁ ተጽእኖ ሊፈጠርባቸው የሚችል ማህበረሰቦች ላይ ስምሪት ለማካሄድ ከፕሮጀክት አጋሮች ወይም የአካባቢ ባለስልጣኖች (ለምሳሌ፡ ሌሎች የግዛት ድርጅቶች እና/ወይም የCambridge ከተማ) ጋር መተባበር።	የረጅም ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች ቡድን ሰንጠረዦችን፣ በራሪ ጽፎችን፣ መልዕክቶችን፣ ወዘተ ጨምሮ ጠንካራ የስምሪት ዕቅዶችን እንዲተገብር ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርጉ። **IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:** የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶች	DCR በአሁኑ ወቅት በመቶዎች ከሚቆጠሩ ህግ አውጪዎች፣ ማዘጋጃ ቤቶች፣ እህት ድርጅቶች እና አጋሮች ጋር ግዛት አቀፍ ግንኙነት የማድረግ ኃላፊነት የተሰጣቸው 5 አስተባባሪዎችን የያዘ ቡድን አለው።
3. የDCR የቋንቋ ተደራሽነት ዕቅድ ከእነዚህ የአሰራር ሂደቶች ጋር መቀናጀቱን ማረጋገጥ።	የአጭር ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ነባር ሰራተኞች **IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:** የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶች	DCR አንዳንድ የቋንቋ ተደራሽነት አገልግሎቶችን ለማቅረብ ቀደም ብሎ ስራ ላይ ያዋላቸው አሰራሮች አሉት።
4. በ EEA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ላይ የተመሰረተ የDCR የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ማዘጋጀት እና መተግበር።	የመካከለኛ ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ነባር ሰራተኞች **IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:** DCRን ጠንካራ ዕቅድ በማዘጋጀት ላይ የሚያግዙ አማካሪዎች	DCR በሂደት ላይ ያለ የውስጥ ስራ ረቂቅ አለው።
5. አንድ ፕሮጀክት ከተጠናቀቀ በኋላ በፕሮጀክቱ የቆይታ ወቅት ውስጥ በሙሉ ከማዘጋጃ ቤቶች፣ የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት፣ አጋሮች እና ድርጅቶች ጋር	የአጭር ጊዜ ወይም የመካከለኛ ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች የድህረ ጥረት ትንተና፣ ክትትል እንዲያካሂድና ሪፖርት እንዲያቀርብ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርጉ።	DCR በአሁኑ ወቅት ከባለድርሻ አካላት ጋር ባሉት ነባር ግንኙነቶች ላይ ተመስርቶ ለፕሮጀክቶች የስምሪት እና ተሳትፎ ዕቅዶች ያዘጋጃል።

የተደረጉ የስምሪትና ግንኙነት ጥረቶችን መገምገም።		**IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:** የሉም	

<u>ምክረ ሀሳብ 4 - ትግበራ:</u> DCR በLongfellow እና በEliot ድልድዮች መካከል ለሚገኘው የMemorial Drive አካባቢ በኮመንዌልዝ ውስጥ ከመሰረተ ልማት ጋር የተገናኙ ችግሮችን ለመፍታት እንደ ሙከራ ለመሰረተ ልማት ችግሮችና በግብረ ኃይሉ በኩል ለተሰበሰበው ግብረ መልስ ለመተግበር ከላይ የተገለጹትን የግንኙነት እና ስምሪት ምክረ ሀሳቦች (ምክረ ሀሳቦች ከ1-3) ይተገብራል።

መነሻ ዐውድ: *DCR በLongfellow እና Eliot ድልድዮች መካከል ላለው የCharles ወንዝ አካባቢ ከላይ በተገለጹት ምክረ ሀሳቦች ውስጥ የተዘረዘሩትን ስትራቴጂዎች/እርምጃዎች መተግበር አለበት። ከዚህ የሙከራ ትግበራ ጥረት የተገኙ ምርጥ አሰራሮችና ትምህርት በግዛቱ ውስጥ ባሉ ተመሳሳይ ችግሮች በሚያጋጥሟቸው ሌሎች ቦታዎች ላይ ሊደገሙ ይችላሉ።*

የጊዜ ሰሌዳ ፍቺዎች: የአጭር ጊዜ = ከ3 ወራት-2 ዓመታት፣ የመካከለኛ ጊዜ = ከ3-5 ዓመታት፣ የረጅም ጊዜ = >5 ዓመታት።

የተመከሩ የትግበራ ስትራቴጂዎች ወይም ድርጊቶች	**የትግበራ የጊዜ ሰሌዳ**	**ትግበራውን ለመደገፍ የሚያስፈልጉ ሀብቶች**	**ተግባራዊ የተደረገ ወይም በሂደት ላይ ያለ**
1. በግብረ ኃይሉ ስብሰባዎች፣ የትኩረት ቡድኖች ወይም የህዝብ ሀሳብ መስጫ ስብሰባዎች ወቅት ከአካባቢው የመሰረተ ልማት ማሻሻያዎች እና እነዚህ ተጽእኖ ሊፈጠርባቸው ለሚችል ማህበረሰቦች ከላይ በተሰጡት ምክረ ሀሳቦች መፍትሄ ሊያገኙ ከሚችሉበት መንገድ ጋር በተያያዘ ለተነሱት ለተለያዩ ኩነቶች የግንኙነት እና ተሳትፎ ዕቅድ ማዘጋጀት። እነዚህ ኩነቶች የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው: ○ የመንገድ መዘጋትን የሚፈልግ	የመካከለኛ ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ለህዝብ ጉዳዮች ከአዳዲስ ባለድርሻ አካላት፣ ተአማኒ የማህበረሰብ ምንጮች፣ እና የተለዩ ተጽእኖ የሚፈጠርባቸው ማህበረሰቦች ጋር ግንኙነቶች መመስረትና ማስቀጠልን፣ እና ሰንጠረዥ፣ በራሪ ጽሁፍ፣ መልዕክቶችን፣ ወዘተ ጨምሮ የተሻሻለ ስምሪት ማቅረብን ጨምሮ ጠንካራ የስምሪት ዕቅዶችን እንዲተገብር ተጨማሪ ድጋፍ የሚያደርጉ። **IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:**	በግብረ ኃይሉ ስራ አማካኝነት DCR ለምርጥ አሰራር ኩነቶች ዝግጅት መረጃ ለመስጠት በCambridge አካባቢ ከሚካሄዱ ፕሮጀክቶች ጋር ተያያዥነት ባላቸው የተወሰኑ ዝግጅቶችና መሰረተ ልማት የግንኙነትና የህዝብ ተሳትፎ ፍላጎቶች ላይ በርካታ ግብረ መልስ ሰብስቧል።

ትልቅ ዝግጅት (ለምሳሌ፡ የCharles ኃላፊ፣ ኮንሰርቶች፣ ወዘተ) ○ የፓርኮች ወይም የመንገድ መስመር፣ ወይም ለጥገና የህዝብ መገኛ ቦታን ጊዜያዊ መዘጋት ሊፈልግ የሚችል አነስተኛ ፕሮጀክት (ለምሳሌ፡ የመንገድ ላይ ውድድሮች፣ ፌስቲቫሎች) ○ ከአንድ በላይ የተሳትፎ ዙሮች ያሉት ትልቅ አዲስ ፕሮጀክት (ለምሳሌ፡ Magazine Beach)		ለምሳሌ፡ የካፒታል ኢንቨስትመንቶችን የሚይዙ፤ የፕሮጀክት የገንዘብ ድጋፍ ያስፈልጋል።	
2. ምን የግንኙነት ስትራቴጂዎች ውጤታማ እንደሆኑ፣ ምን ክፍተቶች አሁንም እንዳልተፈቱ እና የማህበረሰብ አባላት አዲሱን የአሰራር ሂደት እንዴት እንደሚቀበሉት ለመከታተል ግልጽ የግምገማ ማዕቀፍ ማዘጋጀት።	የመካከለኛ ጊዜ (በገንዘብ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ)	**ሰራተኞች:** ነባር ሀብቶች **IT:** የለም **ሌሎች ሀብቶች:** DCRን ጠንካራ የግምገማ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ላይ የሚያግዙ አማካሪዎች	በአሁኑ ወቅት ምንም የግምገማ ማዕቀፍ የለም።

7. የጋራ ሰብሳቢዎቹ የመዝጊያ አስተያየቶች

የCharles ወንዝ ግብረ ኃይል ሥራ በህዝብ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ትርጉም ያለው፣ ግልጽ እና ዘላቂ የማህበረሰብ ተሳትፎ አስፈላጊነትን አረጋግጧል። በተሳትፎ ሂደቱ ወቅት በሙሉ የማህበረሰብ አባላት ወጥነት ባለው መልኩ ግልጽ ግንኙነት፣ ቅድሚያ ግብዓት መስጫ ዕድሎች፣ በግዛት እና የማዘጋጃ ቤት ድርጅቶች መካከል ጠንካራ ትብብር ማድረግ፣ እና በታሪክ ውስጥ በህዝብ የአሰራር ሂደቶች ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ የተወከሉ ማህበረሰቦችን የሚደርሱ የስምሪት አሰራሮች እንደሚያስፈልጉ አጽንኦት ሰጥተዋል።

ምንም እንኳን ግብረ ኃይሉ በህዝብ ሀሳብ መስጫ ስብሰባዎች፣ የትኩረት ቡድኖች፣ የህዝብ ዳሰሳ ጥናቶች፣ የአንድ ለአንድ ውይይቶች፣ የቤት ለቤት ስምሪት፣ እና ከማህበረሰብ አጋሮች ጋር በተደረጉ ቀጥተኛ ውይይቶች አማካኝነት ከፍተኛ የተሳትፎ ጥረት ያደረገ ቢሆንም ይህ ስራ የመነሻ ስራ ብቻ እንደሆነ እንገነዘባለን። እምነት መገንባት፣ ግንኙነቶችን ማጠናከር፣ እና የበለጠ አካታች የሆኑ የተሳትፎ አሰራሮችን ማዘጋጀት በአንድ ብቻ ግብረ ኃይል ወይም የአንድ ዓመት ስምሪት ሊሳኩ አይችሉም። ትርጉም ያለው ተሳትፎ ዘላቂ ኢንቨስትመንት፣ ትኩረት የተደረገበት የአቅም ግንባታ፣ በቂ የገንዘብ ድጋፍ፣ እና የረጅም ጊዜ የማዳመጥ፣ መማርና መቀበል ቁርጠኝነት ይፈልጋል።

በዚህ ሪፖርት ውስጥ የተካተቱት ምክረ ሀሳቦች DCR አንዴት ግንኙነቱን፣ ስምሪቱን እና የህዝብ ተሳትፎ አሰራሮቹን ማጠናከር መጀመር እንደሚችል በተመለከተ ፍኖተ ካርታ ይሰጣሉ። አንዳንድ ማሻሻያዎች አሁን ባሉት ሀብቶች ሊካሄዱ የሚችሉ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ ተጨማሪ ኢንቨስትመንት እና ድርጅታዊ አቅም ይፈልጋሉ። በአንድ ላይ እነዚህ ምክረ ሀሳቦች አሁን ያሉትን ዕድሎች እና በመላው ኮመንዌልዝ ውስጥ ዘላቂነት ያለው ተአማኒና የበለጠ እኩል ተሳትፎን ለመገንባት የሚያስፈልጉ የረጅም ጊዜ ቁርጠኝነቶችን የሚረጋግጥ ተጨባጭ የወደፊት መንገድ ይፈጥራሉ።